የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡» 2ጢሞ. 3፥16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»
መዝ. 118(119)፥130


**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org


**Copyright © 2008**




# ማውጫ

ክፍል ፩


| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት አንድ፦ ደኅንነት ...... | 5 |
| ፩. ደኅንነት ምንድን ነው? ...... | 5 |
| ፪. እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደኅንነት መንገድ ምንድን ነው? ...... | 5 |
| ፫. አንድ ሰው ሲድን በሕይወቱ ምን ምን ይከናወናል? ...... | 6 |
| ፬. አንድ ሰው ስለ መዳኑ ርግጠኛ መሆን ይችላል? ...... | 7 |
| ፭. ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የልጅነት ግንኙነትና ሊኖረን የሚገባ ኅብረት ምንድን ነው? ...... | 7 |
| ፮. ጌታ ያዳነን ለምንድን ነው? ...... | 8 |
| ትምህርት አንድ፡ - ደኅንነት – ጥያቄዎች ...... | 10 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው:: «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው:: ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን::

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል:: ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል:: ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ::

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል:: አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው:: ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን::

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን::





# ክፍል ፩




**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል::»
መዝ. 118(119)፥130**

## ትምህርት አንድ፡- ደኅንነት

### ፩. ደኅንነት ምንድን ነው?

ደኅንነትን በተለያየ መንገድ ልንረዳው እንችላለን:: አንድ ሰው ከመኪና አደጋ ሲተርፍ ከመኪና አደጋ ዳንሁኝ ይላል:: ከአንድ ሕመም ሲፈወስ ከዚያ ሕመም ዳንሁ ይላል::

የእግዚአብሔር ቃል የሚናገርለት ደኅንነት ግን በመጀመሪያ መንፈሳዊ ደኅንነትን የሚመለከት ነው:: አንድ ሰው ሊደርስብት ከነበረው የዘላለም ፍርድና ሞት ሲድን ማለት ነው::

ደኅንነት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በትክክል ለመረዳት ስለ አዳምና ሔዋን መመልከት አስፈላጊ ይሆናል:: እግዚአብሔር አምላክ ፍጥረትን በየመልኩና በየወገኑ ከፈጠረ በኋላ ሰውን የፍጥረት ሁሉ ገዥ አደረገው::

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን መልካም (ኀጢአት የሌለባቸው) አድርጎ እንደ ፈጠራቸው ከእግዚአብሔር ቃል እናያለን ዘፍ. 1÷31፤ መክ. 7÷29:: ሰው መልካም ሆኖ ቢፈጠርም፣ ነጻ ምርጫ ስለ ነበረው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ:: ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ እግዚአብሔር አስቀድሞ አስጠንቅቆት እንደ ነበረ ሁሉ በመንፈስ ምዉት ሆነ:: «መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና::» (ዘፍ. 2÷17)

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ከመተላለፋቸው በፊት፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንደ ልብስ ለብሰው የሚመላለሱ ነበሩ:: ትእዛዙን ከተላለፉ በኋላ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ከላያቸው ተገፈፈ፤ ራቍታቸውን እንደ ሆኑም አስተዋሉ:: ቅጠልንም አገለደሙ (ዘፍ. 3÷7):: <u>በመንፈስ ከእግዚአብሔር ተለዩ፤ ይህም መንፈሳዊ ሞት ነው</u>:: በአዳምና በሔዋን የጀመረው መንፈሳዊ ሞት ለሰዎች ሁሉ ደረሰ (ሮሜ 3÷23፤ ኤፌ. 2÷1-4)::

ስለዚህም ሰው የእግዚአብሔር ነገር የማይገባው (1ቆሮ. 2÷14)፤ ለራሱ ብቻ የሚኖር፣ በራሱ ፈቃድ የሚመላለስና፣ እንደዚሁም የመልካምና የክፉ መለኪያው የራሱ ግላዊ ፈቃድ መሚላትና አለመሚላት ሆነ:: ዐውቆም ይሁን ሳያውቅ የሰይጣንን ፈቃድ የሚፈጽም ሆነ:: ይህም በአዳም በደል ምክንያት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተፈጠረው የጥል ውጠ ት ነው::

### ፪. እግዚአብሔር ያዘጋጀው የደኅንነት መንገድ ምንድን ነው?

ሰው ከአምላኩ መለየቱ መልካም ስላይደለ፣ በአንጻሩ ደግሞ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ በመሆኑ ኀጢአት ሳይቀጣ መታለፍ ስሌለበት፤ የሰው የኀጢአት ዕዳ የሚከፈልበትን <u>የደኅንነት መንገድ እግዚአብሔር</u>





<u>አዘጋጀ</u>:: ይህም፤ እውነትና መንገድ ሕይወትም በመሆን የጥልን ግድግዳ ያፈረሰው አስታራቂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ 3÷16፤ 2ቆሮ. 5÷18-19፤ ዮሐ. 14÷6)::

በአንድ ሰው (በአዳም) ምክንያት ሞት ለሰዎች ሁሉ እንደ ደረሰ፣ በአንዱ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ደግሞ የዘላለም ሕይወት ለሰዎች ሁሉ ደረሰ (ሮሜ 5÷15-21)::

ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፉ የተገፈፈው ጸጋ፣ የእግዚአብሔርን ቃል (ቃለ ወንጌልን) በሚታዘዝበት ጊዜ ይመለስለታል (ኤፌ. 2÷5-9)::

#### ወንጌል የሚከተሉትን በዐጭሩ ይናገራል፡ -

1. ሰው ሁሉ በኀጢአት ምክንያት በመንፈስ የሞተ እንደ ሆነ (ሮሜ 3÷23፤ 6÷23)፣
2. ኀጢአተኛነቱን ዐውቆ ንስሓ መግባት እንዳለበት (ሐዋ. 17÷30)፣
3. ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን እንደ ሞተ የኀጢአታችንን ዕዳ እንደ ከፈለ (ሮሜ 5÷8)፣
4. ሰው ኀጢአተኛነቱን ዐውቆ፣ ንስሓ ገብቶ፣ የክርስቶስን መሥዋዕትነት ከተቀበለ ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት (እንደሚሸጋገር ደኅንነትን እንደሚያገኝ) (ዮሐ. 1÷12፤ 3÷16)::

የእግዚአብሔር ቃል ደኅንነት በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ ይነግረናል::
«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ (ፍርድ) የለባቸውም::» (ሮሜ 8÷1)

«መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና::» (ሐዋ. 4÷12)

«እኔ (ኢየሱስ) መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ <u>በእኔ በቀር</u> ወደ አብ የሚመጣ የለም::» (ዮሐ. 14÷6) «በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፤ ይገባልም፤ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል::» (ዮሐ. 10÷9)

### ፫. አንድ ሰው ሲድን በሕይወቱ ምን ምን ይከናወናል?

1. በመንፈስ ዳግም ይወለዳል (በመንፈስ ዐዲስ ፍጥረት ይሆናል) (1ቆሮ 5÷17፤ ዮሐ. 3÷1-5)፤

2. የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል (ዮሐ. 1÷12)፤
3. ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ይሸጋገራል (1ጴጥ. 2÷9)፤
4. የእግዚአብሔርን ምሕረት ያገኛል (1ጴጥ. 2÷10)፤
   ያለፈ ኀጢአቱ በሙሉ ይቅር ይባላል (1ዮሐ. 1፥7)፤
5. ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ይሸጋገራል (ዮሐ. 3÷16)።

## ፬. አንድ ሰው ስለ መዳኑ ርግጠኛ መሆን ይችላል?

«የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።» (1ዮሐ. 5÷13) አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበለ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስም እንደ ዳነ ይመሰክርለታል። «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።» (ሮሜ 8÷16) ድሮ ሲያደርግ የነበረውን ኀጢአት መጥላትና መራቅ ይጀምራል። ኅሊናውም ኀጢአት በሠራ ቍጥር ወቀሣውን በግልጽ (ከቀድሞው ይበልጥ) ያሰማዋል። በተጨማሪም ስለ ሌሎች መዳን ግድ ይለዋል (2ቆሮ. 5÷18-19)፤ የመንፈስ ፍሬዎችም በሕይወቱ መታየት ይጀምራሉ፤ «ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት።» (ገላ. 5÷22-23)

## ፭. ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የልጅነት ግንኙነትና ሊኖረን የሚገባ ኅብረት ምንድን ነው?

የልጅነት ግንኙነት (Relationship)፤ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ቤተ ሰብ የመሆን ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ሰማያዊ (መንፈሳዊ) አባታችን ነው፤ እኛ ደግሞ ልጆቹ ነን። ይህንን ግንኙነታችንን የእኛ መውደቅና መነሣት፣ መድከምና መበርታት አይለውጠውም። ዘላለማዊ ግንኙነት ነው። ይህንን ግንኙነት ማቋረጥ የምንችለው እኛ ራሳችን ብቻ ነን። በራሳችን ፈቃድ፣ የአንተን አባትነት ከዛሬ ጀምሮ አልፈልግም ብለን የምናደርገውን እያወቅን፣ የእግዚአብሔርን አባትነት ካልካድን በስተቀር እርሱ ለዘላለም አይክደንም። ከእርሱም ሊለየን የሚችል ኀይል የለም (ሮሜ 8÷35-39)።

ኅብረት (Fellowship) ግን ከእግዚአብሔር ጋር በየዕለቱ ሊኖረን የሚገባን የመንፈስ ኅብረት ነው (1ዮሐ. 1÷3)። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት (Fellowship) በኀጢአት ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል (ኢሳ. 59÷1)። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን የአባትና የልጅ ግንኙነት ግን ኀጢአት በሠራን ቍጥር ይሰረዛል ማለት አይደለም። አንድ ወላጅ ደስ የሚሰኝበትም ሆነ የሚያዝንበት ልጅ ሊኖረው እንደሚችል ሁሉ፤ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ፣ ወይም እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ልጅ መሆን እንችላለን። ነገር ግን በኀጢአት በወደቅን ቍጥር ልጅነታችንን ወይም ደኅንነታችንን እናጣለን ማለት አይደለም። በኀጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ሲቋረጥ፣ ቶሎ ብለን በንስሓ የእግዚአብሔርን ምሕረት መቀበልና መንገዳችንን ማስተካከል ይኖርብናል።





በንስሓ ምሕረትን ከተቀበልን በኋላ የሰይጣንን ክስ መስማት የለብንም (1ዮሐ. 1÷7-9፤ 2÷1)።

## ፮. ጌታ ያዳነን ለምንድን ነው?

ጌታ ያዳነን መንግሥተ ሰማያት እንድንገባ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ልክ እንደዳን ከዚህ ዓለም መከራ ወዲያውኑ ቢወስደን ይሻል ነበር። ነገር ግን በመዳንና ወደ መንግሥተ ሰማያት በመግባት መካከል እግዚአብሔር በሕይወታችን ማከናወን የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው?

1. <u>በእርሱ እንድናርፍ ነው</u>

«እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ፣ በልቤም ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ፣ ሸክሜም ቀሊል ነውና።» (ማቴ. 11÷28-30)

«ዕረፉ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁኝ ዕወቁ።» (መዝ. 46÷10) በመታዘዝና በእምነት ወደ ዕረፍቱ እንገባለን። (ዕብ 3÷8-11፤ ዕብ. 3÷18-19፤ ዕብ 4÷1-3፥9-10)

«እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።» (2ጴጥ. 5÷7)

2. <u>ከእርሱ እንድንማር ነው</u>

«... ከእኔም ተማሩ...» (ማቴ 11÷28)
«ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፤ የልጆሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።» (ኢሳ. 54÷13)

«... ማርያም ደግሞ ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች። ... ኢየሱስም መልሶ፣ ... ማርያም መልካም ዕድልን መርጣለች፣ ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።» (ሉቃ 10÷38-42 ክፍሉን በሙሉ ያንብቡ)

<u>የጌታ ጥሪ ቅደም ተከተል</u>

ሀ. ኑ   ለ. ዕረፉ   ሐ. ከእኔም ተማሩ   መ. አገልግሉ

(በእርሱ ሳናርፍና ሳንማር ማገልገል አንችልም)

3. <u>የእርሱ ማደሪያ ለመሆን እንድንሠራ (እንድንቀደስ</u>)

«... መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» (1ጴጥ. 2÷1-5)

«... ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ ዐብራችሁ ትሠራላችሁ።» (ኤፌ. 2÷20-22)

መቀደስም ሆነ መርከስ የሚጀምረው ከልባችን (ከሐሳባችን) ነው።

«በልባችሁ (በአእምሮአችሁ) መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» (ሮሜ 12÷1-2፤ 1ቆሮ. 6÷19-20)

የሚቀድሰን የኢየሱስ ክርስቶስ ደምና የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዕብ. 9÷13-14፤ 1ዮሐ. 1÷7፤ ዮሐ. 17÷17፤ ኤፌ. 5÷25-27)።

4. <u>እርሱን እንድናመሰግን (ለእርሱ ክብር እንድንኖር)</u>

መዝ. 50÷14-15፡23፤ 1ዜና 23÷30-32፤ ሮሜ 1÷21

5. <u>የእርሱን በጎነት ለመንገር (ለመመስከር)</u>
1ጴጥ. 2÷9፤ ሐዋ. 1÷8፤ ማቴ. 5÷14

6. <u>እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የመደበውን ሥራ እንድንሠራ</u> ኤፌ. 2÷10፤ ሐዋ 9÷15፤ 13÷36

7. በአጠቃላይ የደኅንነታችን የመጨረሻ ግብ <u>ክርስቶስን መምሰል</u> ነው።

«... የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአል።» (ሮሜ 8÷29) ክርስቶስን የምንመስለው፣ የሥጋን ምኞት አስወግደን፣ በሕይወታችን እያደገ በሚሄደው የመንፈስ ፍሬ ነው።

«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው። ... የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።» (ገላ. 5÷22-24)

ስለዚህ ጌታን በግል የተቀበልን ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመምሰል ቃሉን በማንበብና በጸሎት እንዲሁም ከአማኞች ጋር ኅብረት በማድረግ በየዕለቱ መትጋት አለብን (ሐዋ. 2÷42፤ ዕብ 10÷24-25)።

«እንግዲህ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ፤ ሥር ሰዳችሁም በእርሱ ታነጹ፤ እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፤ ምስጋናም ይብዛላችሁ።» (ቈላ. 2÷6-7)





## <u>ትምህርት አንድ፡ - ደኅንነት</u>

የመታወቂያ ቍጥር፤______________________________
ስም፤ ____________________________________
አድራሻ፤__________________________________

1. ደኅንነት ክቡርና ቸል ሊባል የማይገባው እንደ ሆነ የእግዚአብሔር ቃል በዕብ 2÷3 «እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንል እንዴት እናመልጣለን?» በማለት ይገልጻል። የሰው ልጅ ደኅንነት ያስፈለገው ለምንድን ነው?

2. ወንጌል የሚያስተላልፋቸው መሠረታውያን መልእክቶች ምንድን ናቸው?

3. ሰው ደኅንነትን እንዲያገኝ፤

   ሀ. እግዚአብሔር ያደረገው ምንድን ነው?
   ለ. ሰው መውሰድ ያለበት ርምጃ ምንድን ነው?

4. ደኅንነትን ያገኘ ሰው በሕይወቱ ሊታዩ ከሚችሉ ለውጦች ዋና ዋናዎቹ ምንድን ናቸው?

5. እግዚአብሔር ሰውን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ያዳነው፤

   ሀ. ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ባለ ግንኙነት እንዲመላለስ ብሎ ነው?
   ለ. የዳነ ሰው እንዲደርስበት እግዚአብሔር የተለመለት (ያቀደለት) የመጨረሻ ግብ ምንድን ነው?

6. ደኅንነትን አግኝተዋል?
   - መልስዎ አዎን አግኝቻለሁ ከሆነ፣ ደኅንነትን እንዳገኙ እንዴት ርግጠኛ መሆን ቻሉ?
   - መልስዎ ደኅንነትን አላገኘሁም ወይም ያገኘሁ አይመስለኝም የሚል ከሆነ፣ ምክንያትዎን ይጻፉ።